

ൠ44-1ൡ

# ጠቃሚ ምክር

## “ውሳኔ መወሰን አቃተኝ” ለሚሉ

እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን ሰው ሊገምተውና ምስጢሩን ሊረዳው ከሚችለው በላይ የሆነ የማሰብ ኃይል ሰጥቶናል። “በምታደርገው ሁሉ እግዚአብሔርን አስቀድም፤ እርሱም በትክክለኛው መንገድ ይመራሃል” (ምሳሌ 3፥6) የሚለው ተስፋው በሕይወታችን ይሠራል። ይህንን ታላቅ የእግዚአብሔር ስጦታ በመጠቀም በሕይወታችን ልዩ ልዩ ውሳኔዎች አስተላልፈናል። ባደረግናቸው ውሳኔዎች ምክንያት የተጠቀምንባቸውና የተጎዳንባቸው ጊዜያት አሉ። የወሰናቸው ውሳኔዎች በተደጋጋሚ ያልጠበቅነውን ዓይነት መጥፎ ውጤቶችን አስገኝተውልን ከሆነ ቀስ በቀስ አዳዲስ ውሳኔዎችን ለማስተላለፍ ወይንም አስፋላጊውን እርምጃ በአስፈላጊው ጊዜ ለመውሰድ እየፈራን እንመጣለን። ውሳኔያችን ጥሩ ውጤቶችን አስገኝቶልን ከሆነ ግን በውሳኔ አሰጣጣችን እያደግን ከመምጣታችንም ሌላ ውሳኔ ለማስተላለፍም ድፍረት ይኖረናል።

በአሁኑ ወቅት የእኛን ውሳኔ የሚጠብቁ ብዙ ዓይነት ሁኔታዎች ላይ እንገኝ ይሆናል። ለምሳሌ፥

የውጪ አገር ሰው ላግባ?
ሥራ ሳይኖረኝ በአሁኑ ሰዓት ትዳር ልያዝ?
ውጪ አገር ሄጄ ልኑር?
ወደ አገሬ ልመለስ?
ወደ አገልግሎት ልግባ?...

እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ውሳኔ ልንሰጥባቸው የሚያስፈልጋቸው የተለያዩ ሁኔታዎች ይኖሩን ይሆናል። በግል ሕይወቴ ከምንጊዜውም የበለጠ መንታ መንገድ ላይ የቆምኩበት ከፍተኛ ውሳኔ ለመውሰን የፈራሁበትና የተጠራጠርኩበት ጊዜ ነበረኝ። ይህን ውሳኔዬ በቀጥታ የሚነካው እኔን ብቻ ሳይሆን ቤተሰቤንም ጭምር ነበር። ጥሩ ውሳኔ ካስተላለፍኩ ከእኔው ጋር ቤተሰቤም ይጠቀማል፤ መጥፎ ውሳኔ ካስተላለፍኩ ደግሞ አሁንም የምጎዳው እኔ ብቻ ሳልሆን ቤተሰቤም ጭምር ይሆናል። ለዚህ ነበር ለመወሰን በጣም የተቸገርኩት። ያም “ጌታዬን በሙሉ ጊዜ ላገልግለው ወይንስ ከዚህ በፊት አገልግለው እንደነበረው በተማርኩት ሙያ ተሰልፌ እየሠራሁ በትርፍ ጊዜዬ ላገልግለው? የሚለው ጥያቄ ነበር።

የመጨረሻውን ውሳኔ ከማድረጌ በፊት ራሴን ብዙ የተለያዩ ጥያቄዎች ጠየቁአለሁ። “ልጀምረው ያሰብኩት አገልግሎት ሌሎች ገብተውበት የተሞከረ ስላልነበረ በድፍረት ዘሎ መግባቱ ያዋጣል? አገልግሎቱን ወስጄ ብጀምር ሊደግፉኝ የሚችሉ ሰዎች ለመሆኑ አሉኝ?” “አብረንህ እንቆማለን” የሚሉኝ ሰዎች ቢኖሩስ ምን ያህል በእነርሱ መታመን እችላለሁ? ልገባበት ያሰብኩት አገልግሎት ደሞዝ ከፋይ ድርጅት የሌለበት ስለሆነ ራሴን የማኖርበት፣ ልጆቼን የማሳድግበት የገንዘብ ድጋፍ ከየት አገኛለሁ?...” እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ጥያቄዎች በአዕምሮዬ ውስጥ ይመላለሱ ነበር። ጥያቄዎች ሁሉ ተገቢ ያልሆኑ አልነበሩም። በሌላ አቅጣጫ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ በውስጤ ልጠራጠረው በማልችለው ሁኔታ “እሺ” ብዬ እንድታዘዝና ወደ አገልግሎት እንድገባ የሚጠራኝ ድምጽ ይሰማኝ ነበር። ለጊዜያዊ ምቾት ስል ብቻ ወይንም በምድራዊ ኑሮዬ ያልተመቸኝስ እንደሆነ ብዬ በመፍራት ብቻ እግዚአብሔርን “እምቢ” በማለት ባለውለታዬንና ከዚህ ያደርሰኝን ጌታዬን ማስቀየሙና ማሳዘኑ እጅግ ከበደኝ።

የመጨረሻ ውሳኔዬ “እሺ” ወደማለቱ ሲያዘነብል፥ የግል ኩራቴ (self pride) እንዳልራመድ አንቆ ያዘኝ። “... አንዳንድ ሰዎች መለሰ ወደ አገልግሎት የገባው ሌላ ሥራ ስላጣ ነው ቢሉህስ? እንዴት ከየሰው በሚሰበስብ በመዋጮ ገንዘብ ለመኖር ትመርጣለህ? የሚረዳህ ሰው ሳታገኝ ቀርተህ ልጆችህ ቢራቡስ? ያስ ደግሞ እንደ እግዚአብሔር ቃል ኃላፊነትህን በመርሳትህ በእግዚአብሔር ፊት ሊያስጠይቅህ አይችልም ወይ?” የሚሉ ጥያቄዎችና ሃሳቦች በአዕምሮዬ ይመላለሱ ጀመር። ያም ሆነ ይህ በመጨረሻ ጌታን ለማገልግለል ወስኜ ሥራዬን ጀመርኩ። በአገልግሎቴም ብዙ ጥሩ ፍሬዎችን በማየቴ የተሳሳተ ውሳኔ እንዳልወሰንኩ ለመረዳት ጊዜ አልፈጀብኝም። የብዙ ሰዎች ሕይወት ሲነካ፣ ብዙዎች ከሞት ወደ ሕይወት ሲመጡ አየሁ። እንደፈራሁት እኔና ቤተሰቤ እስካሁን አልተራብንም። ውሳኔዬም መልካም ፍሬ

የሚያፈራው በሕይወት ባለሁበት ዘመን ብቻ ሳይሆን የምድር ጉዞዬን ጨርሼ ወደ ሰማያዊ ቤቴ ከሄድኩ በኋላም ይቀጥላል። ይህን ማለቴ ግን ውሳኔዬ ምንም ዓይነት ዋጋ አላስከፈለኝም ማለት አይደለም።

ሕጻን ልጁ "ውሳኔ መወሰን" እንዲማርለት የፈለገ አንድ አባት አንድ ዕሁድ ቤተ ክርስትያን ለመሄድ ሲነሳ ለልጁ ሃያ አምስት ሳንቲምና አሥር ሳንቲም ሰጠውና አንደኛውን ለቤተ ክርስትያን እንዲሰጥ ሌላውን ደግሞ ከረሜላ ገዝቶ እንዲበላበት ነገረው። ምን ያህሉን ለቤተክርስትያን እንደሚሰጥ በምን ያህሉ ደግሞ ከረሜላ እንደሚገዛ አልነገረውም። ያንን ውሳኔ ልጁ እንዲወስን ተወለት። ከሰዓት በኋላ ልጁ ምን ዓይነት ውሳኔ እንዳደርገ ለማወቅ ጓጉቶ ምን ያህሉን ለቤተክርስትያን እንደሰጠ ጠየቀው። ልጁም ሲመልስ "መጀመሪያ ሃያ አምስቱን ሳንቲም ለቤተ ክርስትያን ለመስጠትና በአሥር ሳንቲሙ ደግሞ ከረሜላ ለመግዛት አስቤ ነበር። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ 'ማንም የሚሰጥ በደስታ ይስጥ' የሚለው ቃል ትዝ ሲለኝ አሥር ሳንቲሙን ለቤተ ክርስትያን ብሰጠ የበለጠ ደስ እንደሚለኝ ስለተረዳሁ አሥር ሳንቲሙን ሰጠሁ" ሲል ለአባቱ መልስ ሰጠ። አባትየው በዚህ ዕድሜው ልጅ ትክክለኛ ውስኔ ያደርጋል ብሎ ባይገምትም ዓላማው ውሳኔ እንዲያደርግ ለማደፋፈር ነው።

**ውሳኔ የእድገት መሰላል ነው**

በሰው ሕይወት የተሳካ ፍሬን ለማፍራት ከሚያስችል ውሳኔ ለመድረስ ብዙ ጠቃሚ የሆኑ መመሪያዎችን ማግኘት ይጠይቃል። ከጥሩ ውሳኔ ለመድረስ ባለን መሣሪያ ሁሉ መጠቀም ያስፈልገናል። ዓለማችን ሰፊና ለመኖር አስቸጋሪ እየሆነች በሄደች ቁጥር ብዙ ውሳኔ ልንሰጥባቸው የሚገባቸው ጥቃቅንና ትላልቅ የሆኑ ሁኔታዎች ያጋጥሙናል። ዕድገታችንም ከምንወስዳቸው ውሳኔዎች ጋር አብሮ ይሄዳል። ታታሪ የሆኑ ሰዎች በኑሮአቸው ብዙ ጊዜ ዕድገትየሚያሳዩ ናቸው። ምንም ሳይሠሩ የሚፍልጉት ነገር እጃቸው ላይ እንዲቀመጥላቸው ከሚመኙ ሰዎች ይልቅ ትታሪ ሰዎች በሕይወታቸው ውስጥ ብዙ የተለያዩ ውሳኔዎችን ያስተላልፋሉ። በሚያደርጉት "ውሳኔ" ምክንያት አልፎ አልፎ ያልጠበቁት ዓይነት መጥፎ ውጤት አይደርስባቸውም ማለት አይደለም። ይሁን እንጂ "ዕድገት" ያለ ውሳኔ ቁጭ ብሎ ከላይ መና በመጠበቅ ብቻ የሚገኝ አለመሆኑን ስለሚያውቁ አልፎ አልፎ ውጤቱ ጥሩ ባይሆንም ውሳኔን ከመወሰን ወደ ኋላ አይሉም።

**ከውሳኔ ለመድረስ አቋራጭ መንገድ የለም**

በሕይወታቸው ከመንታ መንገድ ሲደርሱ የትኛውን አቅጣጫ እንደሚወስዱ ግራ በመጋባት ምክር የሚፈልጉ ሰዎች አሉ። ይሄም ብልህነት እንጂ ክፋት የለውም። አንዳንድ ሰዎች ግን እግዚአብሔር የሰጣቸውን አዕምሮ በመጠቀም እንዲሁም የእግዚአብሔርን ግፊት ለማግኘት በጸሎትና በጾም በጌታ ፊት በመቃተት ፈንታ አቋራጭ መንገድ ይፈልጋሉ። እነርሱ መጾምና መጸለይ ሲገባቸው፥ የጾመና የጸለየ ሰው ትንቢት እንዲናገርላቸው፣ ራዕይ እንዲያይላቸው ይፈልጋሉ። "እግዚአብሔር ለመሆኑ ስለ እኔ ምን ነግሮሃል? ምን አሳይቶሃል?" ሲሉ ይጨቀጭቁታል። የዓለም ሰዎች ጠንቋይ እንደሚጠይቁ ሁሉ አንዳንድ ክርስትያኖችም የራዕይ ወይንም የትንቢት ስጦታ ያለውን ሰው ሲያሳድዱ እቤታቸው አስመጥተው ሲጋብዙ ይታያሉ። ስጦታው፣ ግብዣው ሲከብድበት ጌታ ባይነግረውም "ጌታ እንዲህ አድርግ ወይንም እኝዲህ ልትሆን ነው ብሎሃል" ብሎ በድፍረት ለመናገር ወደ ኋላ አይልም። የአንዳንድ ክርስትያኖችን የራዕይና የትንቢት ጥማት የተመለከቱ አንዳንድ ጮሌዎች ደግሞ "ጌታ ይህን ነገረኝ፣ ይህን አሳየኝ" በማለት በየሰው ቤት እየዞሩ መብያ ምክንያት ማድረጋቸው የሚይቀር ነው። ይህን ስንል ወደ ውሳኔ እንድንደርስ እግዚአብሔር በትንቢት ወይንም በራዕይ አይናገረንም ማለታችን ሳይሆን ሌሎች ራዕይ እንዲያዩልን የምጠብቅ ከሆነ ስህተት ላይ እንወድቃለን ማለታችን ነው።

1. የተፈጥሮ እውቀት (Common sense)

እግዚአብሔር በሰጠን አዕምሮ መጠቀም ኃጢአት የሚመስላቸው አንዳንድ ሰዎች አሉ። ይህ ልክ አለመሆኑን በተለያየ መንገድ ከዚህ በፊት ለማስተማር ሞክረናል (የሕይወት መስታወት ቁጥር 42ን ይመልከቱ)። የማሰብ ችሎታን የሚሰጥ እግዚአብሔር እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። "ጥበትን ለጠቢባን፣ ዕውቀትንም ለአስተዋዮች የሚሰጥ እርሱ ነው" ይላል (ዳንኤል 2፥21)። እንዲሁም አማኞች እግዚአብሔር በሰጠን የማሰብ ችሎታ መጠቀም እንደሚገባን መጽሐፍ ቅዱስ ያስገነዝበናል። "በዚህ ዓለም የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ጠቢባን መሆን ይገባቸዋል፤ ምክንያቱም ጥበብን ማግኘት ርስትን የመውረስ ያህል ነው" ይላል (መክብብ 7፥1)።
በየቀኑ ውሳኔ የምንሰጥባቸው ትላልቅና ትናንሽ ሁኔታዎች ያጋጥሙናል። አንዳንዶቹ ጊዜ ልንወስድባቸው የሚገቡ ሲሆኑ አብዛኞዎቹ ግን ጥቃቅን በመሆናቸው ቶሎ ቶሎ የምንወስናአቸው ሁነኢታዎች ናቸው። ጸሎት የሚያስፈልጋቸውና

የሚያስፈልጋቸው አሉ። ለምሳሌ “በሚቀጥለው ሳምንት ዕራት አብረን እንድንበላ እቤታችን ጋብዤሃለሁ” የምለው ሰው “ልጸልይበትና እነግርሃለሁ” ብሎ መልስ ቢሰጠኝ ያስቀኛል። ከዚህ ይልቅ “በዚያን ዕለት ፕሮግራሜ ምን እንደሆነ አይቼ ይመቸኝ እንደሆነ እነግርሃለሁ” ቢለኝ ግን የበለጠ ያረካኛል።

አዕምሮአችንን በደንብ ለመጠቀም ራሳችንን ካለማመድን በአንዳንዶቹ ላይ ውሳኔ ለመውሰድ ይህን ያህል አያስቸግረንም። በየጊዜው ከተለያየ ስፍራ በጣም ብዙ የተለያዩ ደብዳቤዎች ይደርሱናል። በብዙዎቹ እጅግ በጣም እንባረካለን። አልፎ አልፎ ደግሞ የሚያስቁ ደብዳቤዎችም ያጋጥሙናል። አንዳንዶቹ በደብዳቤያቸው እግዚአብሔር ጥሩ የኑሮ ጓደኛ እንዳዘጋጅላቸው በመግለጽ ጌታን አመስገነው ይጽፉልናል። ዝቅ ብለው ግን ሥራ እንደሌላቸው፣ የዕለት ምግባቸውን እንኳን የሚያገኙት አንዳንድ ሰዎች እየረዱአቸው እንደሆነ ጨምረው ይገልጹልናል። ለምሳሌ ያህል በቅርቡ አንዱ ከጻፈልን ደብዳቤ በመጠኑ እናካፍላችሁ፤ “…በጥቅምት ወር የጋብቻችንን ሥነ ሥርዓት ለመፈጸም እየጸለይን ነው፤ ነገር ግን ከጋብቻ ባሻገር ያለውን በረከትና ድል አውቆ ጠላት ለሙሽራ የሚያስፈልገውን ጌጣ ጌጥ፣ ወርቅ፣ ሰዓት፣ ሙሉ የሙሽራ ልብስ፣ ለድግሱ ዝግጅት የሚሆነው ገንዘብ ከየት ታመጣለህ? እያለ ይከሰኛል…” ይላል። ሁኔታው በጣም ያስቃል። ይህን ወንድም የከሰሰው እርሱ እንደገለጸው ሰይጣን ሳይሆን “የተፈጥሮ ዕውቀት” (Common sense) ውሳኔው ትክክለኛውን ጊዜ ጠብቆ ያልተደረገ መሆኑን ሲነግረው ነበር። “የተፈጥሮ ዕውቀት” ይህን ወንድም የሚለው “ጋብቻ ግሩም ድንቅ ቢሆንም ጊዜን ካልጠበቀ በረከት በመሆን ፈንታ መርገም ሊሆን ይችላል። ሥራ የለህም፤ እንኳን ሰው ጨምረህ ራስህም የምትበላው የለህም፤ በዚህ ላይ ልጅ ቢወለድ ምን ትሆናለህ?” ነው። ይህን ከላይ የገልጽኩት ወንድም መልሱን ዝቅ ብሎ ሰጥቶናል። “…እኔ የዲያብሎስን ሥራ እያወቅሁ የበረከት ሁሉ ምንጭ ወደሆነው ጌታ ኢየሱስ በእምነት እየጸለይኩ ነው” ይላል። በእምነት መኖር፣ በእምነት መራመድ ድንቅ ነው፤ በእምነት መራመድ የሚያስፈልግበት ጊዜ አለ። ግን “የተፈጥሮ ዕውቀትንም” ማድመጥ የሚያስፈልገን ጊዜ አለ። ቀስ ብሎ በደረጃው ተራምዶ ከፎቅ መውረድ የሚችለው ሰው ቶሎ ለመድረስ “በእምነት ከፎቅ ዘልዬ እወርዳለሁ” በማለት ተከስክሶ ቢሞት ወይንም ከጉዳት ላይ ቢወድቅ ጥፋቱ የራሱ እንጂ የእግዚአብሔር አይደለም።

ሁኔታዎች ሻል ሲሉ ወይንም አንዳንድ ሁኔታዎች ሲመቻቹለት ቆይቶ በማግባት ፈንታ የሥጋው ግፊት ሲያስጨነቀው “የእምነት እርምጃ እወስዳለሁ” ብሎ ማለት በእምነት ስም ከፎቅ ዘሎ ራስን እንደመጉዳት ይቆጠራል። ይሄም በእግዚአብሔር መታመን ሳይሆን እግዚአብሔርን መፈታተን ይሆናል (ማቴዎስ 4፥7)። አንዳንድ አማኞች “እነ እከሌ ሲጋቡ ምንም አልነበራቸውም፤ በእምነት ብቻ እርምጃ ሲወስዱ ተሳካላቸው” በማለት ትክክል ላልሆነው ውሳኔያቸው ድጋፍ ለማግኘት ሲሞክሩ ይታያሉ። እነ “እከሌ” ተሳክቶላቸው ይሆናል። ይሁን እንጂ ለእነርሱ መሳካቱ ለሁሉም ይሳካል ማለት እንዳልሆነ መረዳት ይጠቅማል። “የተፈጥሮ ዕውቀትን” ማዳመጥ ትክክል ያልሆነ እርምጃ እንዳንወስድ ይጠብቀናል።

## 2. በቂ ጊዜ መውሰድ

አስፈላጊ ለሆኑ ነግሮች ውሳኔ ከመስጠታችን በፊት ለራሳችን በቂ ጊዜ መስጠት በጣም አስፈላጊ ነው። በሕይወታቸው ትላልቅ ውሳኔዎችን የወሰዱ አንዳንድ ታላላቅ ሰዎች ከመወሰናቸው በፊት ሁኔታውን በሁለት አቅጣጫ በመመልከት ጥቅሙንና ጉዳቱን ይመዝናሉ። የታወቁት ሳይንቲስት ዶክተር ጆርጅ ካርቨር ከውሳኔ ከመድረሳቸው በፊት ያደርጉት የነበረውን እርምጃዎች አንዱ ሲጽፍ እንዲህ አለ፤ የታወቀው ሳይንቲስት ዶክተር ጆርጅ ካርቨር ውሳኔ ሲወስን በቅደም ተከተል የሚያደርጋቸው ወይንም የሚከተላቸው ነገሮች ነበሩት። መጀመሪያ ስለዚያ ሃሳብ በቂ መረጃ ከየሥፍራው ይሰበስባል። ቀጥሎም ሰዎች ስለዚያ ነገር ምን እንዳሉና ምን እንደሚሉ መረጃ ያጠራቅማል። የሰበሰባቸውን መረጃዎችና እውቀቶች በልቡና በአዕምሮው ውስጥ ጊዜ በመስጠት እንዲብላሉ ያደርጋል። ዶክተር ካርቨር ሁልጊዜ እግዚአብሔር እንዲመራው መጸለይ ልማዱ ነበር። ሁኔታውን ራሱ ሲገልጽ፥ ‘ለረጅም ጊዜ ተሰውሮብኝ የነበረው ነገር ድንገት ብልጭ ይልልኛል። ይህ የሚሆነው በጥናት ላይ እያለሁ ወይንም በማስተማር ላይ ወይንም በጠዋት ጸሎቴ ላይ እያለሁ ይሆናል’ አለ። የሚያስደንቀው ዶክተር ካርቨር ሁልጊዜ “እግዚአብሔር ገለጠልኝ” በማለት ክብሩን ሁሉ ለእግዚአብሔር መስጠቱ ነበር። ለውሳኔያችን በተቻለ መጠን በቂ ጊዜ እንስጠው። ነገር ግን በጥቃቅኑ ሁሉ ጊዜ በማጥፋት ደግሞ የተፈጥሮ ችሎታችንንና ተሰጥዖአችንን እንዳናባክን እንጠንቀቅ። ነገሩን በውስጣችን ካብላላነው በኋላ ውሳኔ ማድረግ በሚያስፈልገን ወቅት ስናመነታ እንወስን። “በጥንቃቄ ዕቅድ አውጥተህ ብትሠራ ብዙ ሀብት ታገኛለህ፤ ያለ ዕቅድ በችኮላ ብትሠራ ግን ትደኸያለህ” ይላል ምሳሌ 21፥5።

.........................................................................................

**በሚቀጥለው ክፍል እስክንገናኝ፥ የጌታ ጸጋና ሰላም ከሁላችን ጋር ይሁን።**